# አገሬ



*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*ሰንፎብኛል ልቤ በሰደት ተቀጣ፤*
*ባንደኛው ሲናፍቅ ባንደኛው እያጣ፤*
*ጊዜ እያንገላታ ያለንን ሲነጥቀን፤*
*ውሃውን !፤*
*አንቺ የቀዳሽውን፤*
*አንቺው ጠጭው ብለን፤*
*ከአገር አምልጠን፤*
*ጥለንሽ ኮብልለን፤*
*ምኑ ተቀበለን ?!*
*ምን ዕድል ገጠመን ?!*
*ምን ዕውቀት ገበየን ?!*
*ምን ንብረት አፈራን?!*

*ልንገርሽ እምዬ፤*
*አገር ገበናዬ፤*
*ማረፊያ ጎጆዬ፤*
*ፍቅሬን እህህ.... እያልሺ....ፍቅርሽን እርቄው፤*
*ናፍቆትሽን በጉያ በልቤ ሸሽጌው፤*
*ሆዴም እንዳይባባ በቂጣ ደልዬው፤*
*ሃዘን ብሰጭቴን በጥርሴ ሸፍኜው፤*
*እኖራለሁ ኑሮ የኑሮ ተላላ፤*
*በወግ ያልታመሰ በወግ ያልተቆላ ::*

*ይኸው በኔ ብሶ......ሁሌ እባዝናለሁ፤*
*ጉልበቴን ጨርሼ ሸንበቆ ሆኛለሁ፤*
*አጥንቴን ከስክሼ እንገዳገዳለሁ፤*
*ስጋዬን ዘልዝዬ በደሜ አጠቅሳለሁ፤*
*እድሜዬን ጋግሬ ሳልበላው አልፋለሁ ።*

*እናም !*
*ልንገርሽ አገሬ፤*
*መመኪያዬ ክብሬ፤*
*ፍቅርሽን ተርቤ፤*
*ናፍቆትሽን ደርቤ፤*
*ሰንደቅሽን አንግቤ፤*
*ካንቺ የራኩበት ቢረዝምም ጊዜያቱ፤*
*አሁንም አልቀረ ባንቺ መመካቱ፤*
*ልቤ አንቺን መራቡ ላንቺ መባባቱ ።*

*ነሐሴ 28 2002 ዓ.ም. (Septembre 3/2010)*

*ከእናት አገራቸው ኢትዮጵያ በስደት ርቀው ለሚንገላቱ ወገኖቼ መታሰቢያ ትሁንልኝ ።*